**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**

# የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበር መመሪያ (የተከለሰ)

መጋቢት 2007

ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## ማውጫ

1. መግቢያ ....4
2. ትርጓሜ ....5
3. የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ዓላማ ....5
4. የአፈጻጸም ስልቶች ....7
5. መርሆዎች ....10
6. የከተማ ጤና ኤ ክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበር ....10
   6.1 የፕሮግራሙ አደረጃጀትና አሰራር ....10
   6.2 የሞዴል ቤተሰብ ስልጠና ....15
   6.3 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ይዘትና የሚተገበርባቸው ስፍራዎች ....18
7. ተግባርና ሀላፊነት ....32
8. የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የድጋፍና ክትትል ማዕቀፍ ....41
   8.1 መረጃዎችን በቋሚነት መመዝገብና ሪፖርት ማድረግ (*Automated*) ....41
   8.2 በቋሚነት መገምገም (Periodic reviews) ....41
   8.3 ድጋፋዊ ክትትልና ኢንስፔክሽን ....42
   8.4 የከተማ ጤና ኤክስቴሽን ፕሮግራም ስኬታማነት አመላካቾች ....44

# 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ በከተሞች የሚኖሩ ህዝቦች በጣም አናሳ ከሆኑባቸው ሀገሮች የምትመደብ ስትሆን 17% ብቻ የሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል በከተሞች ይኖራል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ማዕከለዊ የእስታትሰቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሠረት በአጠቃላይ 952 ከተሞች ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ከተሞች በጣም በፍጥነት እያደጉ ከሚገኙባቸው የአለም ሀገራት ለመመደብ ችላለች፡፡ እ.ኤ.አ በ2050 42% የሚሆነዉ የህብረተሰብ ክፍል በከተሞች ይኖራል ተብሎ ይገመታል፡፡ ፈጣን የሆነ የከተሜነት መጨመር በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ ህዝባዊ ሁኔታዎች ላይ ለውጥ ያስከትላል ተብሎ ይገመታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በበሽታዎች ስርጭት፣ ዓይነትና መንስዔዎች እንዲሁም ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ላይ ተፅዕኖ የሚኖራቸዉ ስለሆነ፣ ሊኖሩ የሚችሉ ለውጦችን ያገናዘበ የጤና ሥርዓት መንደፍ አስፈላጊ ነው፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በኢትዮጵያ ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ከፍተኛ ችግር እያስከተሉ ነው፡፡ የኤች አይ ቪ ስርጭት መጠን ከገጠር አካባቢዎች ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ልዩነት ያለው ሲሆን በከተማ 4.8% እና በገጠር 0.8% ነው፡፡ የቲቢ ስርጭትም ሲታይ ከ100,000 ህዝብ 63 ሰዎች በቲቢ በሽታ ይያዛሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ የእናቶችና የህጻናት የጤና ሁኔታ መሻሻል እየታየ ቢሆንም አሁንም ችግሮችን በሚፈለገዉ መጠን ለመቅረፍ በሃገሪቱ በርካታ ሥራዎችን መሥራት እንደሚጠበቅ ያሳያል፡፡ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ስርጭትም በተለይ በከተሞች አካባቢ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ይገኛል፡፡ በአዲስ አበባ የተካሄደ ጥናት ዉጤት እንደሚያመለክተዉ 51% ያክል ሞት የሚመዘገበዉ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ጋር ተያያዥ በሆኑ የጤና ችግሮች ሲሆን 6% ያክሉ በአደጋ ምክንያት ህይወታቸውን ያጣሉ፡፡ ጥናቱ በአጠቃላይ በአዲስ አበባ ለሚኖረዉ ሞት ዋና ምክንያት በቀዳሚነት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እንደሆኑ ያሳያል፡፡

አራተኛዉ የጤናው ዘርፍ የልማት መርሃ ግብር (2009-2014) ትግበራ ውስጥ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ የነበረው በከተማ የጤና አገልግሎቶችን ማጠናከር እና ማስፋፋት ሲሆን ለዚህም የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን እንደ ቁልፍ ስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መነሻ ያደረገዉ ከገጠሩ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተሞክሮ በመውሰድ ሲሆን ትኩረቱም ጤናን ማበልጸግና በሽታ መከላከል ነው፡፡ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን መሰረታዊ መርህ ቤተሰብን መሠረት ያደረገ የጤና ማበልጸግ፣ በሽታ መከላከልና የቅብብሎሽ ሥርዓትን ማጠናከር ነው፡፡ በዚህ አኳያ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽ ፕሮግራም ትግበራ ሂደትም የተፈለገውን ያህል ባይሆንም፣ የተመዘገቡ ለውጦች መኖራቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለሆነም በትግበራ ወቅት የተስተዋሉ ችግሮችን በመቅረፍ በአፈጻጸም ሂደት የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማካተትና የሃገሪቱ ቀጣይ የጤናው ሴክተር የትራንስፎርሜሽን ዕቅድና የጤና አገልግሎቶች ፍላጎትን መሠረት አድርጎ ክለሳ ማድረግ አስፈልጓል፡፡ በተጨማሪም የከተማ መሠረታዊ ጤና አገልግሎት ዳግም ክለሳ (Urban Primary Health Care Redesign) በመካሄድ ላይ ሲሆን ውጤታማነቱን በማየትም በቀጣይ ወደሁሉም የሀገራችን ከተሞች የሚሰፋ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የከተማ መሠረታዊ ጤና አገልግሎት ዳግም ክለሳ ወደ ሁሉም ከተሞች እስኪሰፋ ድረስ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን በላቀ ደረጃ ለመፈጸም ይህን መመሪያ ክልሎች እንደራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲያደርጉት ይጠበቃል፡፡

በዚህ መመሪያ የፕሮግራሙ ዓላማዎች፣የአፈፃፀም ስልቶች፣ አደረጃጀትና አሠራር፣ የፓኬጆች ይዘት፣ተግባርና ሀላፊነት እንዲሁም የክትትልና ግምገማ አግባቦች ተካተዋል፡፡

## 2. ትርጓሜ

### የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም

የጤና አክስቴንሽን ፕሮግራም  በፓኬጅ መልክ የተዘጋጀ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ዋነኛ አካል ሲሆን ቤተሰብንና ማህበረሰብን ማዕከል በማድረግ በሰለጠኑ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አማካኝነት የሚተገበር ጤናን በማበልፀግና በሽታን በመከላከል ህብረተሰቡ በቂ ዕውቀትና ክህሎት አዳብሮ የራሱን ጤና የሚወስንበትና እርምጃ የሚወስድበት የጤና አገልግሎት ነው፡፡

### ቤተሰብ:

በዚህ ፅሑፍ ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ የአባ/እማወራዎች አባላት ማለት ነው፡፡

### ማህበረሰብ:

ማህበረሰብ ማለት የህዝቦች ስብስብ" ለረጅም ጊዜ አንድ ላይ በተወሰነ መልክዓ ምድር አቀማመጥ  በመኖር ያካበቱት የራሳቸው የሆነ ጠንካራ ትስስርና ተሞክሮ ያላቸው ሕዝቦች ናቸው፡፡ በተጨማሪም አብሮ በመኖር ሂደት በባህል፣በወግ፣ እሴቶች፣ወ.ዘ.ተ ጠንካራ ግንኙነት ያላቸው ማለት ነው፡፡

### የጤና ኤክስቴንሽን ማስፋት ስትራቴጂ

የጤና ማስፋት ስትራቴጂ ማለት በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የተመዘገቡ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር በአንድ ጊዜ ለሁሉም ቤተሰቦች የምናዳርስበት፣ በዚህ ሂደትም ማነቆዎችን የምንለይበትና የምንፈታበት እንዲሁም የማስፈፀም አቅማችንን በመገንባት ሁሉም ቤተሰቦች የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን ቀጣይነት ባለው መልኩ በመተግበር ጤናቸውን እንዲያመርቱ የሚያስችል ስልት ነው፡

### የልማት ሠራዊት

የጤና ልማት ሠራዊት ማለት ከህብረተሰቡ ጀምሮ እስከ ላይኛው አመራር ድረስ ማለትም ህዝቡ፣ ባለሙያውና አመራሩ በአንድ የጋራ አላማ ዙሪያ እንደ አንድ ተሳስሮ በተደራጀ ሁኔታ  ጤና  የማስፋት ስትራቴጂውን  ሥራ ለመተግበር የሚያስችል የማስፈጸም አቅም ማለት ነው፡፡

## 3. የከተማ ጤና  ኤክስቴንሽን ዓላማ

### ዋና አላማ

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዋና ዓለማ ቤተሰብንና ማህበረሰብን ማዕከል በማድረግ ፍትሃዊና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ለከተማው የህብረተሰብ ክፍል ማዳረስ ነው፡፡

### ዝርዝር አላማዎች

- ጥራቱን የጠበቀ መሰረታዊ የጤና አገልግሎትን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ሙሉ በሙሉ ማዳረስ፣
- የህብረተሰቡን ንቃተ ጤና በማሳደግ ጤናማ አስተሳሰብና ባህሪ በመፍጠር የማህበረሰቡን ጤናን የማጎልበትና በሽታን የመከላከል ክህሎትና የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነትን መጨመር፣
- ህብረተሰቡን መሠረት ያደረገ የጤና አገልግሎት የቅብብሎሽ ሥርዓት ማዳበር።

## 4. የአፈጻጸም ስልቶች

**የማህበረሰብ ተሳትፎን ማጎልበት፡-** የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተግባራዊነት በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ጥረት ብቻ የሚሳካ ባለመሆኑ ለተግባራዊነቱ የልማት ሠራዊት በመገንባትና ሕብረተሰቡን በማደራጀት የጤና ልማት ሥራዎችን ማከናወን የግድ ነው፡፡ በመሆኑም የልማት ሠራዊት መገንባት ህብረተሰቡ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን በባለቤትነት እንዲይዝና ጤናውን እንዲያመርት ያስችላል፣በፕሮግራሙ የተያዙ ግቦችንም በተሻለ ፍጥነትና ጥራት ማሳካት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የተለየዩ ህብረተሰብ አደረጃጀቶችን ለምሳሌ የወጣቶችና የሴቶች ማህበራት ፣ በአከባቢው ያሉ እድር ማህበራትን በመጠቀም የማህበረሰብ ተሳትፎን ማጎልበትና የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀምን ማሻሻል፡፡

**ዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ፡-** ግብ ጥሎ መሥራት የእቅድ አፈፃፀሙ ከየት ተነስቶ የት ለመድረስና ምን ውጤት መቼ ማግኘት እንደሚቻል በቀላሉ ለመረዳትና ለመከታተል እንዲሁም በእቅድ አፈፃፀም ሂደት የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን በየደረጃው ለመለየትና ለመፍታት የሚያስችል ስልት ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ የእቅድ ክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ በማዘጋጀት የሚያስፈልገውን ግብ በወቅቱና በሚጠበቀው ደረጃ ማከናወን ይገባል፡፡ በዚህ ሂደት በየደረጃው የተመዘገቡ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋት የፕሮግራሙን ስኬታማነት በዘላቂነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ጥራት ያለው ደረጃውን የጠበቀ የመረጃ ልውውጥና አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት፡፡

**ተከታታይነት ያለው የስራ ላይና የሙያ ማሻሻያ ስልጠና መስጠት፡-** የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን በብቃት እንዲተገብሩና ለህብረተሰቡ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ተከታታይነት ያለው የሥራ ላይ ስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በተቀናጀ የማጠናከሪያ ስልጠና ወቅቱን ጠብቆ ማሰልጠን ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ሲከናወኑ የነበሩትን አገልግሎቶች ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሚሰጠው የጤና አገልግሎት በይዘትም ሆነ ጥራቱን ለማሻሻል የሠራተኞችን እውቀትና ክህሎት በረጅም ጊዜ ስልጠና ለማሳደግ ስልት ይቀየሳል፡፡

**ቅንጅታዊ አሠራርን ማስፈን፡-** የጤና ጉዳይ ከጤናው ሴክተር ውጭ ያሉ የሴክተር መሥሪያ ቤቶችንና የልማት አጋሮችን ድጋፍና አስተዋጽኦ የሚጠይቅ ነው፡፡ በተለይም በታችኛው ደረጃ (ማህበረሰቡን ባሳተፈ መልኩ) የሚኖረው ቅንጅታዊ አሠራር አስፈላጊነቱ እጅግ የላቀ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ደረጃ የሚሠሩ ባለድርሻ አካላት መረጃን በመለዋወጥና በመጋራት፣የልምድ ልውውጥ መድረክን በመፍጠር፣የጋራ ዓላማን ለማሳካት ሀብትን በአግባቡና በቁጠባ በመጠቀም፣ በእቅድ፣ በትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ በማሳተፍ የሚታቀዱ የጤና ልማት ግቦችን ለማሳካት ቅንጅታዊ አሠራርን ማስፈን ተገቢ ነው፡፡

**ፍትሃዊና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት መስጠት፡-** በከተማ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ነባራዊ ሁኔታ ከጤና፣ገቢና የትምህርት ደረጃ አንጻር ሲታይ በጣም የተለያዩ ደረጃ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጁ ትኩረት የሚሰጣቸዉን የህብረተሰብ ክፍሎች በመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ

ደረጃውን የጠበቀ የጤና ማበልጸግ፣ በሽታን መከላከልና መሰረታዊ የፈዉስ ህክምና አገልግሎቶችን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**የተቀናጀ የቅብብሎሽ ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፡-** የተቀናጀ የቅብብሎሽ ስርዓት መዘርጋትና መተግበር ለተሳለጠ የጤና አገልግሎት  ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከጤና ጣቢያ ጋር ያለውን የቅብብሎሽ ስርዓት በማጠናከር  የጤና ጣቢያ አገልግሎት የሚሹትን በመለየት ወደ  ጤና ጣቢያ መላክና የጤና ጣቢያውም ወቅቱን የጠበቀ ግብረመልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

## የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበር የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ

**ራዕይ**

**በኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ የሚኖር ጤናማ አምራችና የበለፀገ ማህበረሰብ ተፈጥሮ ማየት፤**

↑

**ግብ**

ቤተሰብና ማህበረሰብ ተኮር የሆነውን የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን በመተግበር በኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦችን የጤና ሁኔታ ማሻሻል፣

↑

**ዝርዝር ዓላማዎች**

- ጥራቱን የጠበቀ መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ሙሉ በሙሉ ማዳረስ፣
- የህብረተሰቡን ንቃተ ጤና በማሳደግ ጤናማ አስተሳሰብና ባህሪ በመፍጠር የማህበረሰቡን የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት መጨመር፣
- ህብረተሰቡን መሠረት ያደረገ የጤና አገልግሎት የቅብብሎሽ ሥርዓት ማዳበር

↑

**የአተገባበር ስልቶች**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| የህብረተሰብ ተሳትፎን ማጎልበት | ቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከር | ተከታታይ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መሥራት | ፍትሃዊ የጤና አገልግሎት መስጠት | የአገልግሎት ጥራትን ማሻሻል | ክትትልና ግምገማ ማጠናከር |

## 5. መርሆዎች

**መከላከልን ትኩረት ያደረገ የጤና አገልግሎት**:- ፕሮግራሙ በዋናነት ትኩረት የሚያደርገው በሽታን የመከላከልና ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን የማበልጸግ ልምድን ማበረታታት ነው፡፡ በህብረተሰቡ ዘንድ ወሳኝ የሆኑ መሠረታዊ የህክምናና ምርመራ አገልግሎቶችም ይሰጣሉ፡፡ በተጨማሪም በሽታዎችን መለየትና ለህክምና ወደ ሚቀጥለው የጤና ድርጅት በፍጥነት መላክ አንዱ የፕሮግራሙ ተግባር ይሆናል፡፡

**ቤተሰብ ተኮር አልግሎት**:- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በቤተሰብ፣በወጣት ማእከላት፣በትምህርት ቤቶችና እንዲሁም በማበረሰብ ደረጃ የሚሰጥ ሲሆን በዋናነት ግን ቤተሰብን ትኩረት ያደርጋል፡፡

**የቡድን ስራ (Team approach)**:- ሁሉም ቤተሰብ/ግለሰብ በሁሉም ደረጃ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የጤና አልግሎት ማግኘቱን ለማረጋገጥና የጤና ሥራ የቡድን ሥራ እንደመሆኑ መጠን በማህበረሰብ ውስጥ የሚሠሩ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና በጤና ጣቢያ የሚሠሩ ባለሙያዎች እንደ አንድ ቡድን በመሆን የጤና አገልግሎት ለህብረተሰቡ ይሰጣሉ፡፡

**የማህበረሰብ ተሳትፎ**:- ፕሮግራሙ ህብረተሰቡን በሁሉም ደረጃዎች ማለትም በእቅድ ዝግጅት፣በትግበራና በግምገማ ወቅት በተደራጀ አኳኋን እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

**ፍትሀዊ የጤና አገልግሎት**:- የተለየ ፍላጎትና አኗኗር ያላቸው የህበረተሰብ ክፍሎችን በማካተት ለሁሉም የጤና አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግና ጤናማ ህበረተሰብ መፍጠር ዓላማው ነው፡፡

**ፈጠራና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም**:- ፕሮግራሙ ተገቢና ፈጠራዊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመቀየስና በመሞከር ይስፋፋል፡፡ ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርግ የፈጠራ ውጤት ይዘው ለሚመጡ አካላትም ማነቃቅያና እውቅና ይሰጣል

**ጥራት ያለው አገልግሎት**:- ያለውን አቅም አሟጦ በመጠቀም ጥራት ያለው የጤና አልግሎት በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ የሚሰጥበት ሁኔታ ይረጋገጣል፡፡

## 6. የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበር

### 6.1 የፕሮግራሙ አደረጃጀትና አሰራር

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ቤተሰብንና ማህበረሰብን ማዕከል አድርጎ ጤናን የማበልፀግና በሽታን በመከላከል ላይ ትኩረት በመስጠት የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡ ይህም በሀገሪቱ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ

ሥርዓት የመጀመሪያ እርከን በሆነው በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ውስጥ ከጤና ጣቢያ ጋር ቅርብ ትስስር ያለውና በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡

ከዚህ ቀደም የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የሥራ ሃላፊነት ለቀበሌ ተስጥቶ ነበር፡፡ ነገር ግን በአፈፃፀም ሂደት የተስተዋሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ባለሙያዎች ተጠሪነት ሙሉ በሙሉ ለጤና ጣቢያ ይሆናል፡፡ የቀበሌ አስተዳደር በቀበሌው ውስጥ የሚከናወኑ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ስራዎችን በጋራ የማቀድ፣ የመከታተልና የመገምገም ስራዎችን ይሰራል፡፡ ለስራው ቅልጥፍናና ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሥራ ቦታ የተመቻቸ እንዲሆን ለማስቻል የቀበሌው አስተዳደር በቂ የስራ ክፍል ህብረተሰቡን በማስተባበር ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ በጤና ጣቢያና በቀበሌዎች መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ለማጠናከርና የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን አፈፃፀም ለማሻሻል ጤና ጣቢያው ከ ቀበሌዎች ጋር አጠቃላይ ግምገማ በየወሩ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ በግምገማው ወቅት በእያንዳንዱ ቀበሌ ያለውን የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮገራም አፈፃፀም ከዕቅድ አንጻር መገምገምና አቅጣጫ ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡፡

ለሁለት ጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎች ቢያንስ አንድ የጤና ጣቢያ ሙያተኛ ተጠሪ ሆኖ መመደብ ይኖርበታል፤ ተከታታይነት ባለው መልኩ ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎቹ ድጋፍ ይሰጣል፤

ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ ባለሙያዎች ለምሳሌ አዋላጅ ነርስ በጤና ጣቢያው ዕቅድ ተዘጋጅቶ ጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎችን መደገፍ ይኖርባቸዋል፤


በጤና ጣቢያው የጤና ጣቢያ ሙያተኞች ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሚሰጡትን የድጋፍና ክትትል ሥራ የሚያስተባብር አንድ ተጠሪ ባለሙያ (Focal Person) ይመደባል፤ የዚህ ባለሙያ ተጠሪነት ለጤና ጣቢያው ዳይሬክተር/ሀላፊ ይሆናል፡፡

የድጋፍና ክትትል ስራ የሚያስተባብር ባለሙያ (Focal Person) ዋና ሥራ የድጋፋዊ ክትትል ፕሮግራም/ሥራን ያስተባብራል፣ በፕሮግራሙ ላይም ለእያንዳንዱ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ቢያንስ በየሳምንቱ ድጋፋዊ ክትትል መደረጉን ያረጋግጣል፤ ለድጋፋዊ ክትትሉ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች መሟላታቸውንም ያረጋገጣል፡፡

የጤና ጣቢያ ባለሙያው ድጋፋዊ ክትትሉን በሚያደርግበት ወቅት የተመደበበትን ሙሉ የሥራ ቀን ከጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ጋር በማሳለፍ ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል፡፡

በአንዳንድ ቦታዎች የከተማ ጤና ጣቢያዎች ለአካባቢው የገጠር ቀበሌዎች አገልግሎት የሚሰጡ ከሆኑ ለገጠር ቀበሌዎች/ጤና ኬላዎች ከዚህ በፊት የወጣውን የጤና ጣቢያና ጤና ኬላ ትስስር መመሪያና የገጠር ጤና ኤክስቴንሽ ፕሮግራም አተገባበር መመሪያን ተከትለው ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

**የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አደረጃጀትና አሠራርሥዕላዊ መግለጫ**




የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ቁጥር እንደከተማው የህዝብ ብዛት የሚለያይ ሲሆን አንድ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያ በአጠቃላይ ለ500 ቤተሰብ፣ አገልግሎት ትሰጣለች፡፡ ይህ ሲባል በሷ የሥራ ክልል ውስጥ ያሉ ሁሉንም 500 ቤተሰብ እኩል ጊዜና ትኩረት ትሰጣለች ማለት ሳይሆን የነዚህን ቤተሰቦች መሠረታዊ መረጃ በመሰብሰብ እንደ ጤና ሁኔታቸው መመደብና ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለይታ አገልግሎት ትሰጣለች ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ አገልግሎቱን የምትሰጥ ከሆነ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ማዳረስ ትችላለች፡፡ አንድ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ በቀን በአማካይ እስከ አስር ቤተሰቦች በመጎብኘት አገልግሎት መስጠት ትችላለች፡፡ በተጨማሪም በቀበሌው የተመደቡት የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ፕሮግራም በማውጣት በቀበሌው ውስጥ በሚገኙት ትምህርት ቤቶችና ወጣት ማዕከላት ሁሉ በየተራ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

## ቅድሚያ የሚሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እንዴት መለየት ይቻላል?

የከተማ ጤና ኤክስስቴንሽን አገልግሎት ፓኬጅ በጅምላ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ከመስጠት ይልቅ ቤተሰቦች ወይም የቤተሰብ አባላትን እንደ ጤና ሁኔታቸው በመመደብ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ቅድሚያ እንዲሰጥ ተደርጎ መሰጠት አለበት። ህብረተሰቡን እንደ ጤና ሁኔታቸው እና እንደሚያስፈልጋቸው የጤና አገልግሎት ለመመደብ መስፈርቶችን መጠቀም ያስፈልጋል። የጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎች የያዙትን ቤተሰብ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መስፈርት ተጠቅመው መመደብ ይችላሉ።

1. የጤና ክብካቤና ክትትል በጣም ለሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች የቤት ለቤት ጉብኝት ማድረግ (ለምሳሌ፡ ከፍለው መታከም የማይችሉ፣ ነፍሰ ጡር እናቶች፣ ከ5 ዓመት በታች ህጻናት፣ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ታመሙ ህሙማን
2. ማህበረሰቡን መሠረት ያደረገ የመስክ ላይ የጤና አገልግሎት (ትምህርት ቤቶች፣ከሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት የስራ ቦታዎችን መጎብኘት)።
3. የበሽታዎችን ስርጭት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የቤተሰብ ምድብ በመስራት ተጠቃሚዎች እንደ አጋላጭ ሁኔታቸው፣ እንደ በሽታውና እንደ ገቢ ደረጃቸው ተመድበው ቅድሚያ ይሠጣቸዋል።

ምድብ I - ነፍሰ ጡር እናቶችና ከ5 ዓመት በታች ያሉ ሕፃናት
ምድብ II - በተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች የተጠቁ የህብረተሰብ ክፍሎች (ኤች አይ. ቪ/ኤድስ፣ ቲቢ፣ የስኳር፣ የልብ፣ የካንሰር ህመምና አስም የመሳሰሉት…)
ምድብ III - ሌሎች (በምድብ I እና II ያልተመደቡ የህብረተሰብ ክፍል፣ እድሜያቸው የገፉና ህጻናት ከ6-14 ዓመትና በምድብ I ያለተመደቡ በዚህ ምድብ ይመደባሉ።

ሌላው አመዳደብ በገቢ መጠናቸው/ሃብታቸውን መሠረት ይሆናል። ለዚህም የሚያገለግል ዝርዝር መስፈርት ይዘጋጃል።

ምድብ ሀ. -ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው
ምድብ ለ. - መካከለኛ ገቢ ያላቸው
ምድብ ሐ. - ከፍተኛ ገቢ ያላቸው

ከላይ ያሉ የሁለቱ ምድቦች ጥምረት ምድብ ሀ፣ለ እና ሐ፤ ምድብ I፣ II እና III ቤተሰቦች ይሠጣሉ። ምድብ Iሀ እና ምድብ IIሀ አባወራዎች ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ሲሆኑ ቀጥሎ በምድብ ለ ስር ላሉት ቅድሚያ ይሰጣል።

| ሁሉም ምድቦች | ሀ ዝቅተኛ ገቢ ደረጃ (1st and 2nd) | ለ መካከለኛ ገቢ ደረጃ | ሐ ከፍተኛ ገቢ ደረጃ |
|---|---|---|---|
| I፡ ነፍሰ ጡር እናቶችና ከ5 ዓመት በታች ህጻናት | ምድብ Iሀ (በመጀመሪያ ደረጃ ቅድሚያ የሚሠጣቸው) | ምድብ Iለ | ምድብ Iሐ |


| | | | |
|---|---|---|---|
| II:አጣዳፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች (ስኳር, የልብ ህመም, ካንሰር, አስም) | ምድብ IIሀ<br>(በሁለተኛ ደረጃ ቅድሚያ የሚሠጣቸው) | ምድብ IIለ | ምድብ IIሐ |
| III: ሌሎች (በምድብ I እና II ያልተመደቡ የህብረተሰብ ክፍሎች እድሜያቸው የገፋና ህፃናት ከ6 — 14 ዓመት)ና የመሳሰሉት በዚህ ምድብ ይመደባሉ:: | ምድብ IIIሀ | ምድብ IIIለ | ምድብ IIIሐ |

*__ማስታወሻ:__ ከላይ በሰንጠረዥ 1 እስከ 3 የተገለፁት አገልግሎት ተጠቃሚዎች በመኖሪያ ቤታቸው የሐይጂንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ሥራዎች ተቀናጅተው የሚተገበሩ ይሆናል።*

| ሳምንታዊ በማህበረሰብ/ቤተሰብ ደረጃ የሚሰሩ ተግባራት መርሃ ግብር እንደሚከተው መሆን ይኖርበታል | |
|---|---|
| የቤት ለቤት ጉብኘት -ለ ምድብ I | በሳምንት ሁለት ጊዜ /በወር 8 ቀናት (ማክሰኞና ሀሙስ) |
| የቤት ለቤት ጉብኘት -ለ ምድብ II | በሳምንት አንድ ጊዜ /በወር 4 ቀናት (እሮብ) |
| የት/ቤት ጤና | በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ (ሰኞ ጠዋት) |
| ወጣቶች ማዕከል | በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ (ሰኞ ከሰዓት) |
| በሌሎች ምድብ ያሉ አባወራዎች/የህብረተሰብ ክፍል-ለምድብ III | እንደ አስፈላጊነቱ |
| በጤና ጣቢያ ዝግጅት /ግምገማ / ሪፖርት ማድረግ | አንድ ቀን - አርብ (ከሰዓት) |

*__ማስታወሻ:__ ሳምንታዊ በማህበረሰብ/ቤተሰብ ደረጃ የሚሰሩ ተግባራት መርሃ ግብር እንደ አስፈላጊነቱ ማሸጋሸግ ይቻላል።*

## ትኩረት የሚሹ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ልየታ አካሄድ ስዕላዊ መግለጫ




## 6.2 የሞዴል ቤተሰብ ስልጠና

የሞዴል ቤተሰብ ስልጠና የማስፋት ስትራቴጂን ተከትሎ የሚከናወን ሲሆን የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በቀበሌ/ቀጠና ደረጃ ለ1ለ5 ትስስርና ልማት ቡድን መሪዎች የክህሎት ስልጠና በመስጠትና ሞዴል እንዲሆኑ በማድረግ በቀጣይነት በልማት ቡድንና በ1ለ5 ትስስር አማካይነት ሁሉም ቤተሰብ በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ አፈፃጸማቸው ሞዴል ሆነው የራሳቸውን ጤና የሚያመርቱበት አካሄድ ይሆናል፡፡

በቀበሌ/ቀጠና ደረጃ አፈፃፀማቸው መሠረት ደረጃ ተሰጥቷቸው የ1ለ5 መሪ ተብለው በልማት ቡድን የተመረጡ ግንባር ቀደም ሴቶች በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና በጤና ጣቢያ ባለሙያዎች አማካኝነት ለ15 ቀናት በቀን ለ4 ሰዓት በድምሩ ለ60 ሰዓታት የክህሎት ሥልጠና ይወስዳሉ፤ በሥልጠናው ጊዜና ከዚያም በኋላ በተግባር ፓኬጆቹን በቤታቸው ይተገብራሉ፤ፓኬጆቹን ሲያሟሉ በሞዴልነት ይመረቃሉ፡፡ ሆኖም ከላይ የተጠቀሰው ለሙሉ ስልጠና የሚፈጀው ሰአት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደሰልጣኞቹ በሰአት የመገኘት፣ የትምህርት አቀባበልና የስራ ሁኔታ እየታየ የስልጠና ቀናት ማጠር ወይም መርዘም ይችላል፡፡

የ1ለ5 ትስስር መሪዎች በስራቸው ከሚገኙ ቤተሰቦች ጋር ለሁለት ቀናት በፓኬጆቹ አተገባበር ዙሪያ ውይይት በማድረግ የትስስራቸውንና የየግል እቅዳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ የፓኬጆች ትግበራን የጊዜ ሰሌዳ ያስቀምጣሉ፤ በተቀመጠው እቅድና የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የ1ለ5 መሪዎች ሳይቆራረጥ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ሁሉንም ቤተሰቦች የሚመለከታቸውን ሁሉንም ፓኬጆች በመፈፀም ሞዴል ሆነው እንዲመረቁ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መሠረት ባጭር ጊዜ ሁሉም ቤተሰብ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ሞዴል ሆነው እንዲመረቁ ማድረግ ይቻላል፡፡ ሞዴል ሆነው የተመረቁ ቤተሰቦች ወደ ኋላ እንዳይመለሱ በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በመታገዝ የ1ለ5 መሪዎች ቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

**ሰንጠረዥ ፡- የልማት ቡድንና የአንድ ለአምስት መሪዎች ስልጠና መርኃ ግብር**

| ቀን | የፓኬጅ ዓይነት | የሚፈጀው ሰዓት |
|---|---|---|
| 1 | የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ፓኬጅ | 4 |
| 2 | የስርዓተ ምግብፓኬጅ | 4 |
| 3 | የወጣቶች ተዋልዶ ጤና ፓኬጅ | 4 |
| 4 | እናቶችና ህጻናት ጤና ፓኬጅ | 4 |
| 5 | የክትባት አገልግሎት ፓኬጅ | 4 |
| 6 | የወባ መከላከልና መቆጣጠር ፓኬጅ | 4 |
| 7 | የቲቢና ሥጋ ደዌ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ፓኬጅ | 4 |
| 8 | የኤች.አይ.ቪ./ኤድስና ሌሎች አባላዘር በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ፓኬጅ | 4 |
| 9 | የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ ፓኬጅ | 4 |
| 10 | ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጣር ፓኬጅ | 4 |
| 11 | አእምሮ ጤና ፓኬጅ | 4 |
| 12 | የግል ንጽሕናና የመኖሪያ አከባቢ ጤና አጠባበቅ ፓኬጅ | 4 |
| 13 | የመፀዳጃ ቤት አሰራርና አጠቃቀም ፓኬጅ | 4 |
| 14 | የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ፓኬጅ | 4 |
| 15 | የመጠጥ ውኃና የምግብ ንጽሕና አያያዝና አጠቃቀም ፓኬጅ | 4 |
| አጠቃላይ የዝግጅት ምዕራፍ ስልጠና ሰዓት | | 60 |

*የጤና አጠባበቅ ትምህርት ፓኬጅ ከላይ በተጠቀሱት ፓኬጆች ተቀናጅቶ የሚሰጥ ይሆናል፡፡*

## *የሞዴል ቤተሰብ ምረቃ መስፈርት*

ቤተሰብ በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ሞዴል ሆኖ ለመመረቅ ከሚከተሉት መስፈርቶች መካከል የሚመለከታቸውን ሁሉም ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

1. የንድፈ ሀሳብና የሠርቶ ማሳያ ስልጠና ካጠናቀቁ
2. ለህፃናት አስፈላጊ የሆኑ ሁሉንም የክትባት አይነት ካስከተቡ
3. ከሁለት አመት በታች ያሉ ህፃናት የእድገት ክትትል ካደረጉ
4. በቤት ውስጥ አዮዲን ያለው ጨው የሚጠቀሙ ከሆነ
5. ለቤተሰብ እቅድ ታላሚ ሆነው ተጠቃሚ ከሆኑ
6. ነፍሰ ጡር የሆነች እናት የቅደመ ወሊድ ክትትል ካደረገች
7. ወላድ የሆነች እናት የወሊድ አገልግሎት በሰለጠነ ባለሙያ ካገኘች
8. አራስ የሆነች እናት የድህረ ወሊድ ክትትል ካደረገች
9. ለመኝታ አጎበር ታላሚ ሆነው አዘውትረው ከተጠቀሙ
10. በወባ ተጋላጭ አካባቢ እየኖሩ በወባ መከላከል የአከባቢ ቁጥጥር ሥራዎች ላይ ከተሳተፉ
11. በወባ ተጋላጭ አካባቢ እየኖሩ የፀረ ወባ ኬሚካል ቤታቸውን ካስረጩ
12. የመፀዳጃ ቤት በአግባቡ ሁሉም የቤተሰብ አባላት አዘውተረው ከተጠቀሙ

13. የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ካላቸውና በአግባቡ ከተጠቀሙ
14. ቤትን በንጽህና ከያዙ
15. የመኖሪያ ቤት አካባቢ/ግቢ ንፅህና ሲታይ በትክክል ከተያዘ
16. ከመኖሪያ ቤት የተለየ ማብሰያ ቤት ኖሯቸው የሚጠቀሙ
17. ከቤት ውጪ ለሚኖሩ እንስሳት መኖሪያ ቤት ለይተው ካዘጋጁ
18. ጤናማ ሆኖ ለመኖር ሆነ ከበሽታ ለመፈወስ ያለ ፍላጎትና የሚወሰድ ተግባር (በየሰአቱ፣ በየጊዜውና በየወቅቱ የጤና ሁኔታ ምርመራና ሕክምና የሚያደርጉ ከሆነ)

## 6.3 የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ይዘትና የሚተገበርባቸው ስፍራዎች

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ጤና ማበልጸግን፣ በሽታን መከላከልንና በጣም ወሳኝ የሆኑ የህክምና አገልግሎቶች በተለያዩ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ደረጃዎች አቀናጅቶ መዘርጋትን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የቤተሰብ ጤና ፓኬጅ፣ የበሽታዎች እና ድንገተኛ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ፓኬጅ እንዲሁም የሀይጅንና የአካባቢ ጤና አገልግሎት ፓኬጅን ቤት ለቤት፣ በማህበረሰብ ደረጃ፣ ትምህርት ቤትና በወጣት ማዕከላት የተለያዩ የመግባቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም የግንዘቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ይሠራሉ፡፡

<table>
<tr><th>ፓኬጆችና አገልግሎቶች</th><th>የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች</th><th>አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ</th><th>አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች</th></tr>
<tr><td colspan="4">1. የቤተሰብ ጤና ፓኬጆች</td></tr>
<tr><td colspan="4">1.1 የእናቶች ጤና</td></tr>
<tr><td colspan="4">ቅድመ ወሊድ አገልግሎት</td></tr>
<tr><td>ስለ እናቶችና ህፃናት ጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት</td><td>ቤተሰብና ህብረተሰብ</td><td rowspan="8">ቤት ለቤት፣ማህበረሰብ<br><br>ቤት ለቤት፣ማህበረሰብ</td><td rowspan="9">የምክር አገልግሎት መስጫ መመሪያ (የቤተሰብ ጤና መመሪያና ሌሎች ባህሪ ለውጥ ለማምጣት የሚረዱ ፣ ወደ ሚቀጥለው ጤና ድርጅት መላኪያ ቅጽ፣,የደም ግፊት መለኪያ መሳሪያ, የኤች አይ ቪ/ኤድስ መመርመሪያ ኪቶች, የአልጋ አጎበር ,አይረን ካፕሱል ,</td></tr>
<tr><td>ስለ እናቶች ስነ ምግብ ሁኔታ፣ ከወሊድ በፊት መደረግ ስለሚገባው ቅድመ ዝግጅት፣ ሊከሰት ስለሚችለው የተወሳሰበ የጤና ችግሮች፣ ስለወሊድና አዲስ ለሚወለድ ህፃን መደረግ ስለሚገባው እንክብካቤ የምክር አገልግሎት መስጠት</td><td>እርጉዝ እናትና ባለቤት</td></tr>
<tr><td>አጠቃላይ ስለ ሁኔታው የሚገልፅ ታሪክ መውሰድ እንዲሁም የአካላዊ ምርመራ/ ፍተሻ (Phisical Examination) የደም ግፊትንም ጭምር</td><td rowspan="6">እርጉዝ እናት</td></tr>
<tr><td>የእርግዝና ምርመራ ማድረግ</td></tr>
<tr><td>የሽንት ምርመራ ማድረግ</td></tr>
<tr><td>አደገኛ የሆኑ ምልክቶችን መለየትና ወደ ጤና ጣቢያ መላክ</td></tr>
<tr><td>የአልጋ አጎበር እንደ አስፈላጊነቱ መስጠት</td></tr>
<tr><td>አይረን ፎሌት መስጠት</td></tr>
<tr><td>ለአባለዘር በሽታ ኤቸ አይ ቪ/ኤድስን ጨምሮ ምርመራ / ልየታ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ</td><td>እርጉዝ እናት</td><td></td></tr>
</table>

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| ለተኮር ቅድመ ወሊድ ምርመራ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ | እርጉዝ እናት | | |
| ከእናት ወደ ልጅ የኤች አይ ቪ ኤድስ እንዳይተላለፍ የመከላከል (PMTCT ) አገልግሎትን በተመለከተ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ | እርጉዝ እናት፣አባወራ | | |
| የክትትል ሥራዎችሥራዎችንሥራዎችንና መድሀኒት ያቋረጡትን መለየትና ወደ ጤና ጣቢያ መላክ | እርጉዝ እናት | | |
| **ወሊድና ድህረ ወሊድ አገልግሎት** | | | |
| በድንገተኛ ሁኒታ ወሊድ ለሚያጋጥማቸው እናቶች ወደ አቅራቢያ ጤና ተቋም እንዲደርሱ ለማስቻል አምቡላንስ አገልግሎት ማመቻቸት | ምጥ ላይ ያለች እናት | ቤት ለቤት | የህፃን መመዘኛና መላኪያ ሪፈራል ፎርም፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣ የሙቀት መለኪያ፣የወሊድ መከላከያ |
| በሰለጠኑ ባለሙያዎች በጤና ድርጅት ደረጃ የወሊድ አልግሎት እንዲያገኙ መላክ | ምጥ ላይ ያለች እናት | | |
| በቅድመ ወሊድ እና ድህረ ወሊድ ለሚያጋጥሙ የተወሳሰቡ ችግሮች ክትትልና ምርመራ  ለማግኘት ወደ ሚቀጥለው የጤና ድርጅት መላክ | እናት | | |
| ድህረ ወሊድና አዲስ የተወለደ ህፃን እንክብካቤ | በቅርብ ጊዜ የወለደች እናት፣ጨቅላ ህጻን | | |
| በአንደኛው፣በሶስተኛውና በሰባተኛው ቀናት የጊዜ ሰሊዳ በማውጣት ቤት ለቤት በመሄድ  ድህረ ወሊድ ክትትል ማድረግ | | | ተመሳሳይ |

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| ከድህረ ወሊድ በኂላ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት (የምክርና የወሊድ መከላከያ) መስጠት | | | |
| ለጨቅላ ህፃን ጤና ክትትል ማድረግ፣ ወደ አቅራቢያው ጤና ጣቢያ መላክ | | | |
| **የህፃናት ጤና አገልግሎት** | | | |
| **የልጆች በሽታ ህክምናና ክትትል** | | | |
| ስለአፍና አይን ጤና አጠባበቅ፣ የግል ንጽህና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት | ተማሪዎች | ት/ቤት | የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣ሪፈራል ፎርም |
| አጠቃላይ አካላዊ ምርመራ (physical examination) ማድረግ, አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልፅ ታሪክ መውሰድና ለሌሎች የልጆች በሽታ ሁኔታ ምርመራ ወደ አቅራቢያው ጤና ጣቢያ መላክ | ከአምስት አመት በታች ያሉ ልጆች | | |
| የታመሙ ልጆችን ወደ አቅራቢያው ጤና ጣቢያ ከመላክ በፊት ተገቢውን ህክምናና ክብካቤ ማድረግ | | ቤት ለቤት፣ት/ቤት፣ማህበረሰብ | |
| ህክምና እየወሰዱ ያሉ ሆነ መውሰድ የሚገባቸው ህጻናትን ጨምሮ ከህክምና አገልግሎት ጋር ቁርኝት በመፍጠር ክትትል ማድረግ | | | |
| **ሥነ ምግብ** | | | |
| ሥነ ምግብን አስመልክቶ የጤና ትምህርት መስጠት | ከአምስት አመት በታች ያሉ ልጆች | በቤተሰብና ፣ማህበረሰብበ፣ትምህርት ቤት | የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች , ሜትር፣ ቫይታሚን A ፣ የጸረ አንጀት ትላትል መድሃኒት, ቁመትና ክብደት |
| እድገት ክትትል ማድረግ | ከ2 እና ከ5 ዓመት ያሉ | | |

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| | ልጆች | | መለኪያ, ሜትር, ቫይታሚን-ኤ ካፕሱል, ሚቤንዳዞል ኪኒን |
| ተጨማሪ ምግብ አዘገጃጀት ሠርቶ ማሳያ መሥራት | ከስድስት ወር እስከ 2 ዓመት ያሉ ልጆች | | |
| ህብረተሰቡ የሚጠቀመው በአዮዲን፣ በብረት ማዕድናት እንዲሁም በቫይታሚን ኤ የበለጸጉ ምግቦች መሆናቸውን መከታተልና ስለ አጠቃቀማቸው ማስተማር | ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት፣እርጉዝ እናቶች፣ወጣቶች | | |
| የፀረ-አንጀት ጥገኛ ትላትል መድኃኒት እና የቫይታሚን ኤ እደላ መሰጠት | ከ6-59 ወራት ለሆኑ ህፃናት ቫይታሚን ኤ እና ከ2-5 ዓመት ለሆኑ ህፃናት | ቤት ለቤት፣ማህበረሰብበ፣ትምህርት ቤት | |
| በከፍተኛ የምግብ አለመመጣጠን የተጎዱ ህፃናትን መለየት፣ ለህክምና ወደ አቅራቢያው ጤና ጣቢያ መላክ | ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት | | |
| **የክትባት አገልግሎት** | | | |
| ክትባት ዙሪያ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት | ቤተሰብ | ቤት ለቤት፣ማህበረሰብ | የቀበሌ/ቀጠና ዝርዝር መረጃ፣የትምህር መርጃ መሳሪያ፣ወደ ጤና ተቋም መላኪያ ቅጽ |
| ክትባት ያቋረጡ ህፃናትን መፈላለግና ወደ ጤና ጣቢያ መላክ | ከ1 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት | | |
| በጤና ተቋማት የክትባት አገልግሎት ያላገኙ ህፃናትን በማፈላለግና ክትትል በማድረግ ክትባት እንዲያገኙ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ | ከ1 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት | | |
| ለመደበኛ የክትባት አገልግሎት ህፃናትን ወደ ጤና ተቋም መላክ | ከ1 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት | | |
| **ቤተሰብ እቅድ** | | | |
| ስለ ቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ሁኔታ የጤና መረጃ/የምክር አገልግሎት | በመውለድ እድሜ ክልል ለሚገኙ ሴቶች (ከ18-49 | | ግንዛቤ ማስጨበጫ ማቴሪያሎች፣የቤተሰብ እቅድ መመሪያ፣ |

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| መስጠት | ዓመት) | | የቤተሰብ እቅድ (የወሊድ መቆጣጠሪያ ክኒን፣ ዲፖና ኮንደም) ወደ ጤና ተቋም መላኪያ ቅጽ |
| በተለያየ ምክንያት ከጤና ተቋማት የወሊድ መቆጣጠሪያ ክኒን፣ዲፖና ኮንደም አገልግሎቶችን ማግኘት ላልቻሉ አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎት መስጠትና ለክትትል ወደ ጤና ጣቢያ መላክ | በመውለድ እድሜ ክልል ለሚገኙ ሴቶች (ከ18-49 ዓመት) | | |
| ከላይ ከተጠቀሱት የቤተሰብ እቅድ አይነቶች ውጪ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶች ፈላጊዎችን ወደ ጤና ተቋም መላክ | በመውለድ እድሜ ክልል ለሚገኙ ሴቶች (ከ18-49 ዓመት) | | |
| **የወጣቶች ተዋልዶ ጤና አገልግሎት** | | | |
| ለወጣት ወንዶችና ሴቶች የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት | ወጣት ወንዶችና ሴቶች | ቤት ለቤት፣ ወጣት ማዕከላትና በትምህርት ቤት | የመረጃ የማስተማሪያና የተግባቦት መሳሪያዎች / የባህሪ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የተግባቦት መሳሪያዎች ፣ የኅልማሶች ወጣቶች ተዋልዶ ጤና መመሪያ ፣ የመላኪያ ቅጽ፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ ክኒን፣ ዲፖና ኮንደም… (ቤተሰብ እቅድ መስጫ ኪት) |
| በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ፣ጥንቃቄ ያለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ በኤች አይ ቪ ኤድስ/የአባላዘር በሽታዎች እና በቅድመ ነፍሰ ጡር መሆን በተመለከተ የምክር አገልግሎት መስጠት | | | |
| ኮንደምና ሌሎች የቤተሰብ ዕቅድ የአገልግሎት ዘዴዎችን ማቅረብ | | | |
| ለውርጃና ከውርጃ በኂላ ላሉ ክብካቤዎች ወደ ጤና ተቋማት መላክ | | | |
| ለሁሉም የወጣቶች ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች የአባላዘር በሽታዎችን ልየታና ክብካቤን ጨምሮ ወደ ጤና ተቋማት መላክ | | | |

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| **2. የበሽታዎች እና ድንገተኛ አደጋዎች መከላከል** | | | |
| ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች | | | |
| ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት | ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ከፍተኛ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች | ቤት ለቤት፣ማህበረሰብ | የማስተማሪያና የተግባቦት መሳሪያዎች፣የደም ግፊት መለኪያ መሳሪያ፣ Dip- stick፣ ሪፈራል ፎርም፣ ሚዛን |
| የደም ግፊት መለኪያ መሳሪያ በመጠቀም ደም ግፊትን መለካት | ለደም ግፊት ከፍተኛ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች | | |
| የስኳር በሽታን በሽታው በሚያሳያቸው ምልክቶችና የሽንት ምርመራ በማድረግ ልየታ ማካሄድ | በስኳር በሽታ በከፍተኛ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች | | |
| የጡት ካንሰር ልየታ ማድረግ | በመውለድ እድሜ ክልል ላይ የሚገኙ ሴቶች | | |
| የደም ግፊትና የስኳር ህመምተኞች የህክምና ክትትል/ቁርኘት እንዲያደርጉ የምክር አገልግሎት መስጠት | በህክምና ላይ ያሉ የደም ግፊትና የስኳር በሽታ ህመምተኞች | | |
| የደም ግፊትና የስኳር ህመምተኞችን በመለየት ወደ ጤና ተቋም መላክ | የደም ግፍትና የስኳር ህመምተኞች | | |
| ለካንሰርና ሌሎች አጣዳፊ ያልሆኑ በሽታዎች የሚከተሉትን አገልግሎቶች መስጠት፡<br>1. ምርመራና ሪፈራል<br>2. የምክር አገልግሎት<br>3. ህክምናውን በአግባቡና በትክክል እንዲወስዱ ማገዝ<br>4. ህመምን ማከምና ሌሎች የቤት ለቤት እንክብካቤ | የካንሰር ህሙማን | | ትምህርት መርጃ ቁሳቁሶች፣ የህመም ማስታገሻ መድሃኒት፣ሪፈራል ፎርም |

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| ለአዕምሮ ጤና የሚከተሉትን አገልግሎቶች መስጠት<br>1. የምክር አገልግሎት<br>2. በአዕምሮ ህሙማን አያያዝ በኩል ቤተሰብን መርዳት<br>3. ህክምናውን በትክክልና በአግባቡ እንዲወስዱ መርዳት<br>4. ሪፈራልና ከጤና ተቋም ትስስር መፍጠር | የአዕምሮ ህሙማን፣ ተንከባካቢ/ቤተሰብ | ቤት ለቤት፣ማህበረሰብ | የትምህርት መርጃ መሳሪያ፣ የሪፈራል ፎርም |
| **ተላላፊ በሽታዎች** | | | |
| በኤች አይ ቪ ዙሪያ የጤና ትምህርት መስጠት | ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች/ህብረተሰብ ክፍሎች | ቤት ለቤት ፣ወጣት ማዕከላትና በትምህርት ቤት | የመረጃ፣ የማስተማሪያና የተግባቦት ማሳሪያዎች፣ የኤች አይ ቪ መመርመሪያ ኪት፣ ስለምርመራና ምክር አገልግሎት አሰጣጥ የሚገልጽ መመሪያ ወደ ጤና ተቋም መላኪያ ቅጽ |
| የኤች አይ ቪ ኤድስ የምክርና የምርመራ አገልግሎት መስጠት | ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች/ህብረተሰብ ክፍሎች | ቤት ለቤት፣ወጣት ማዕከላት | |
| የቅድመ ART/ART አገልግሎት እንዲያገኙ ወደ ጤና ተቋም መላክ | በምርምራ በኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ የሆኑ ህሙማን | | |
| ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ሰዎች የART ህክምና ቁርኝት እንዲያደርጉ የምክር አገልግሎት መስጠት | በህክምና ላይ ያሉ ኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ያለባቸው ሰዎች | ቤት ለቤት | |
| ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ሰዎችን የተለያዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ማድረግ/መላክ | ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ሰዎች | | |
| ለአባላዘር በሽታዎች ልየታ ማድረግ | ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች | ቤት ለቤት ፣ወጣት ማዕከላት | |
| ቲቢን በተመለከተ የጤና ትምህርት መስጠት | ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል | ቤት ለቤት፣ ወጣት ማዕከላት፣ ትምህርት ቤት እና ማህበረሰቡ ሰብሰብ ብሎ በሚገኝባቸው | |

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| | | ቦታዎች | |
| የቲቢ ተጠርጣሪ ህሙማንን ልየታ ማድረግ | ሁሉም ህብረተሰብ፣ ከቲቢ ህሙማን ጋር ግንኙነት ላላቸው እንዲሁም ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ሰዎች | በቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ወጣት ማዕከላትና ትምህርት ቤት | የመረጃ፣ የማስተማሪያና የተግባቦት ማሳሪያዎች |
| የቲቢ ህሙማን የህክምና ቁርኝት እንዲያደርጉ የምክር አገልግሎት መስጠትና መከታተል | በህክምና ላይ ያሉ የቲቢ ህሙማን | ቤት ለቤት | ሪፈራል ፎርም |
| በወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ላይ የጤና ትምህርት መስጠት | ሁሉም ህበረተሰብ | ቤት ለቤት፣ወጣት ማዕከላትና ትምህርት ቤት | የትምህርት መርጃ ማሳሪያዎች፣የፀረ ትንኝ የመኝታ አጎበር፣ፈጣን የመመርመሪያ ኪት፣ፕሮቶኮል፣ የወባ መድኃኒቶች |
| ስለየፀረ ትንኝ የመኝታ አጎበር አጠቃቀምና ጠቀሜታ ማስተዋወቅ | ሁሉም ህበረተሰብ | ቤት ለቤት፣ማህበረሰብ | |
| ፈጣን የምርመራ ኪት በመጠቀም የወባ ምርመራ ማድረግ | ትኩሳት ያለባቸውን ህሙማን | | |
| ለወባ ህሙማን ህክምና መስጠት | በፈጣን መመርመሪያ ኪት ፖዘቲቭ ለሆኑ ህሙማን | | |
| **በማይድን በሽታ ለታመሙ ህሙማን** | | | |
| 1. በማይድን በሽታ ለታመሙ ህሙማን እንክብካቤ ማድረግ<br>2. ቤተሰብን ፊዚዮቴራፒ ላይ ትምህርት መስጠት<br>3. ህመም የማከም አገልግሎት መስጠት<br>4. ህሙማን በጤና ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ከፈለጉ በቅብብሎሽ ቅጽ ወደ ጤና ተቋም መላክ | በማይድን በሽታ ለታመሙ ህሙማን | ቤት ለቤት | የትምህርት መርጃ መሳሪያ፣የሪፈራል ፎርም፣ ህመም ማስታገሻ መድሃኒት፣ የቤት ለቤት ህክምና ክብካቤ መስጫ ኪት |

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| **የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጠትና ድንገተኛ አደጋዎችን መከላከል** | | | |
| ስለመጀመሪያ ህክምና ርዳታ የጤና ትምህርት መስጠት<br>ከህብረተሰቡ ለተውጣጡ ሰዎች ስለመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ አሰጣጥ ስልጠና በመስጠት በአደጋ ጊዜ ወይም ለድንገተኛ ህመም እርዳታ እንዲያደርጉ ማስቻል<br>ከቅድመ ሆስፒታል የድንገተኛ ሕክምና ጋር ያለውን ቁርኝት ማጠናከር<br>ስለትራፊክ አደጋ መከላከል ማስተማር | ከህበረተሰቡ ለተውጣጡ ሰዎች | ማህበረሰብ፣ ሥራ ቦታ | የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣ የመጀመሪያ ህክምና ርዳታ ለመስጠት የሚያግዝ ኪት |
| የመጀመሪያ ህክምና ርዳታ አገልግሎቶችን መስጠት | በድንገተኛ አደጋ የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች | | |
| **3. የአካባቢ ጤና አጠባበቅ** | | | |
| **የመጸዳጃ ቤት አሠራርና አጠቃቀም** | | | |

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| የመጸዳጃ ቤት አሠራር፣ ሽፋንና በአግባቡ አጠቃቀምን በተመለከተ የሃይጅን የምክርና የማስተዋወቅ ሥራዎችን መሥራት | ለሁሉም ማኅበረሰብ በተለይም መጸዳጃ ቤት ለሌላቸው የአባወራዎች/እማወራዎችና የቤተሰብ አባላት፣ የተሻሻለ መጸዳጃ ቤት ለሌላቸውና የመጸዳጃ ቤት አጠቃቀም ችግር ላለባቸው ማኅበረሰቦች | በቤተሰብ፣ወጣት ማዕከላትና ትምህርት ቤት | የሥራ ማጣቀሻዎችና የበህሪ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የተግባቦት መሳሪያዎች |
| የግል፣ የጋራና የሕዝብ የመጸዳጃ ቤቶችን ለመገንባት፣ ሽፋን ለማሳደግና ጥራትን ለማሻሻል  የማኅበረሰብ ንቅናቄ ማካሄድ | ሁሉም ማኅበረሰብ በተለይም መጸዳጃ ቤት የሌላቸው አባወራዎች/አማወራዎች | በቤተሰብና ሕዝብ የሚሰባሰብባቸው ቦታዎች ለምሳሌ የገበያ ቦታዎች፣ የትራንስፖርት መናሀሪያዎች፣ መንገድ ዳር | |
| የሕዝብና የጋራ መጸዳጃ ቤቶችን አጠጋገንና አጠቃቀም/አያያዝ በተመለከተ ትምህርት መስጠት | አባወራዎች/እማወራዎች፣ የመጸዳጃ ቤት አስተዳደር ኮሚቴ አባላት | የአንድ ቋት የውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሀይጅን አገልግሎት ያላቸው ቤተሰቦችና ሕዝብ የሚሰበሰብባቸው አካባቢዎች | |
| አገልግሎቱን በቅድሚያ/በአስቸኳይ ማግኘት ያለባቸውን ቤተሰቦች አገልግሎቱን ከሚሰጡ ባለድርሻ አካላት ጋር ማገናኘት | የመጸዳጃ ቤት የሞላባቸው፣ ከመሙላቱ የተነሳ ወደ አካባቢው የሚፈስ፣ የሰው ጤና የሚያውክ እና በማስመጠጥ ወይም በሌላ ዘዴ የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት ለማግኘት የሚጠባበቁ አባወራዎች/እማወራዎች | ቤት ለቤት | |
| የመጸዳጃ ቤት አገልግሎትን ለማግኘት የሚፈልጉ ቤተሰቦችን ከመጸዳጃ ቤትና ከእጅ መታጠብ ቁሳቁስ ቴክኖሎጂ አማራጭ አቅራቢ ከሆኑ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዝ ጋር ማገናኘት | የመጸዳጃ ቤት ቴክኖሎጂ አማራጭ የሚፈልጉ አባወራዎች/እማወራዎች | ቤተሰቦች | |

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| **የምግብና የውኃ ንጽህና አያያዝ** | | | |
| በማስተማርና በሠርቶ ማሳያ በማሳየት የንጹህ ውኃ መጠጥ አያያዝና ህክምና አሰጣጥን በተመለከተ ማኅበረሰቡን ማስተማርና ሠርቶ ማሳያ በማዘጋጀት መስጠት | ለሁሉም ማኅበረሰብ በተለይም ሴቶች | ቤት ለቤት፣ወጣት ማዕከላትና ትምህርት ቤት | የሥራ ማጣቀሻዎች፣የቤት ውስጥ ውኃ ለማከም የሚያገለግሉ ኬሚካሎች እና የበህሪ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የተግባቦት መሳሪያዎች |
| የምግብ ደህንነት አጠባበቅና ሃይጅን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መሥራት | ሁሉም ማኅበረሰብ በተለይም ከ5 ዓመት በታች ያሉ ህፃናት፣ ነፍሰ ጡር ሴቶች፣ ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለባቸው ሰዎችና የቲቢ ህሙማን | ቤት ለቤት | |
| የቤት ውስጥ ውኃ ማከም ኬሚካልን ለሚፈልጉ ቤተሰቦች አገልግሎቱን ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር ትስስር መፍጠር/ማገናኘት | የቤት ውስጥ ውኃ ማከም ኬሚካልን የሚፈልጉ አባወራዎች/እማወራዎች | በቤተሰብ | |
| **የግልና አካባቢ ጤና ንጽህና አጠባበቅ** | | | |
| የቤት ንጽህና አጠበበቅና በቤት ውስጥ የአየር ብክለትን በተመለከተ ማኅበረሰቡን ማስተማርና ሠርቶ ማሳያ በማዘጋጀት ስለቤትና አካባቢ ንጽህና አያያዝ ማሳየት | ሁሉም ማኅበረሰብ በተለይም ዝቅተኛ የኢኮኖሚ አቅም ያላቸው እና በተጨናነቀ /በተፋፈገ አካባቢ የሚኖሩ፣ ነፍሰ ጡር ሴቶች፣ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት | በቤተሰብ | የሥራ ማጣቀሻዎች፣ የባህሪ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የተግባቦት መሳሪያዎች |
| በወሳኝ ጊዜያት እጅ የመታጠብ ልምድ እንዲዳብር ሠርቶ ማሳያ በማዘጋጀት ማስተማር | ሁሉም ማኅበረሰብ፣ በተለይም አባዎራዎች/እማዎራዎች ከ5 ዓመት በታች ህፃናት ያሉዋቸው ሴቶች፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው | በቤተሰብ፣ ወጣት ማዕከላትና ትምህርት ቤት | የሥራ ማጣቀሻዎች፣ የባህሪ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የተግባቦት መሳሪያዎች ፣የእጅ መታጠቢያ ሠርቶ ማሳያ ለመሥራት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ለምሳሌ ሳሙና፣ የላስቲክ ጠርሙስ፣ የእጅ መታጠቢያ ዕቃዎች.... |

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| | ያለባቸው ሰዎች፣የትምህርት ቤት ህፃናትና ወጣት ማዕከላት | | |
| ቤተሰቦች ከመጸዳጃ ቤት አጠገብ/አካባቢ የእጅ መታጠቢያ ውኃ፣ ሳሙና/አመድ በማስቀመጥ እጃቸውን እንዲታጠቡ ድጋፍ ማድረግ | ሁሉም ማህበረሰብ | በቤተሰብ፣ ወጣት ማዕከላትና ትምህርት ቤት | የእጅ መታጠቢያ እቃዎች፣ ሳሙና/አመድና ውኃ |
| የእጅ መታጠብን በተመለከተ የማኅበረሰብ ዘመቻ ማካሄድ | የትምህርት ቤት ህፃናትና ወጣቶች | በወጣት ማዕከላት፣ ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው አካባቢዎችና በትምህርት ቤቶች | |
| **የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ** | | | |
| ስለየደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ማኅበረሰቡን የምክርና የማስተዋወቅ አገልግሎት መስጠት | ሁሉም ማኅበረሰብ በተለይም ህፃናት ያሉዋቸው ቤተሰቦች፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ሰዎች፣ ነፍሰ ጡር ሴቶች እና በተጨናነቀ /በተፋፈገ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች | በቤተሰብ፣ በወጣት ማዕከላት፣ በሥራ ቦታዎች እና ትምህርት ቤቶች | በከተማ ሳኒቴሽንና ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ላይ ያሉ ፖሊሲዎች፣ደንቦችና መመሪያዎች/ደረጃዎች |
| ሕዝብ የሚሰበሰብባቸውን አካባቢዎች በመለየት ለምሳሌ መንገድ፣ ሕዝብ የሚጸዳዳባቸው ቦታዎች… መደበኛ የሆነ የሳኒቴሽን የጽዳት ዘመቻ ማካሄድ | ሁሉም ማኅበረሰብ | በቤተሰብ፣ በወጣት ማዕከላት፣ በሥራ ቦታዎች፣የሕዝብ ተቋማት እና ትምህርት ቤቶች | |

| ፓኬጆችና አገልግሎቶች | የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|---|---|
| ቤተሰቦችን የመጀመሪያ ደረጃ የደረቅ ቆሻሻዎችን ከሚያሰባስቡ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ጋር ማገናኘት | ደረቅ ቆሻሻዎችን ለማስወገድ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የሚፈልጉ አባ/እማዎራዎች | በቤተሰብ፣ በወጣት ማዕከላት፣ ትምህርት ቤቶች | |
| ቤተሰቦች በአግባብ ቦታ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ በአግባቡ እንዲሠሩና እንዲጠቀሙ ድጋፍ ማድረግ ለምሳሌ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስረጊያ ጉድጓድ፣ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያና ማብላያ ጋን/ገንዳ እንዲሠሩ ወዘተ | የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ያላቸው አባ/እማዎራዎች | በቤተሰብ፣ በወጣት ማዕከላት፣ ትምህርት ቤቶች | |
| የሥራ ቦታዎች የሥራ ደህንነት ለጤና አስጊ አለመሆናቸውን የቁጥጥር ሥራ መሥራት | በአካባቢው ያሉ የሥራ ቦታዎች ለምሳሌ ኢንዱስትሪ፣ የፋብሪካ ቦታዎች | የሥራ ቦታዎች | |
| ጉዳዩ ከሚመለከታቸው (ጤና ተቆጣጣሪዎች፣ ማዘጋጃ ቤት ወዘተ ) ጋር በመተባበር በምግብና መጠጥ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲሁም በንግድ ቦታዎች የንጽህና ቁጥጥር ማካሄድ | በማኅበረሰቡ አካባቢ ያሉ የምግብና መጠጥ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት እንዲሁም ሌሎች የንግድ ማዕከላት | የሥራ ቦታዎች | |

## 7. ተግባርና ሀላፊነት

**የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተግባርና ሃላፊነት**

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ለማስፈፀም የልማት ሠራዊት ግንባታን ቁልፍ ተግባሩ አድርጎ መንቀሳቀስ፣
- የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድን ማጠናከር፣
- መመሪያዎችንና ለፕሮግራሙ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ማዘጋጀት ተፈፃሚነታቸውንም መከታተል፣
- ከፌዴራል መንግስት ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች ከክልል ምክር ቤቶች ከጤና ቢሮዎችና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሠራርንአሠራርን በማጠናከር ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መሳካት በጋራ መሥራት፣ አስፈላጊ ግብአቶችንም ማሟላት፣
- በየክልሉ የተዋቀሩ ኮማንድ ፖስቶችን መደገፍ፣ መከታተል፣ የመረጃ ልውውጥ ማድረግና በቅንጅት መሥራት፣
- በየዓመቱ ሁሉንም ክልሎችና አጋር ድርጅቶችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ፤ በዚህም በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም የተሻለ ደረጃ ላላቸውና የላቀ አስተዋፅዖ ላበረከቱ አካላት እውቅናና ማበረታቻ መስጠት፣
- የድጋፍዊ ክትትል ሥራዎችን ማከናወን፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች/ባለሙያዎች የሥራ ላይ ስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ትምህርት የሚያገኙበትን ሥርዓት መዘርጋት፤ ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- የፕሮግራሙን አፈጻጸም ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ማካሄድ/ማስተባበር፣
- ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- ወጥነት ያላቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ፣ ሪፖርት ማቅረቢያ፣ የክትትልና የግምገማ ቅጾችን ማዘጋጀትና ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣
- የጤና አጠባበቅ መርጃ መሳሪያዎችን፣ የስልጠና ማኑዋሎችንና የማጣቀሻ መጽሐፎችን ማዘጋጀት፣

**የክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ/ከተማ መስተዳድር ተግባርና ሀላፊነት**

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ለማስፈፀም ልማት ሠራዊትግንባታን ቁልፍ ተግባሩ አድርጎ ይንቀሳቀሳል
- የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድን ማጠናከር፣
- በክልሉ የተዋቀሩ ኮማንድ ፖስቶችን መደገፍ፣ መከታተል፣ የመረጃ ልውውጥ ማድረግና በቅንጅት መሥራት፣ አስፈላጊ ግብአቶችንም ማሟላት፣
- በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን መሠረት በማድረግ እንደየክልሉ ነባራዊ ሁኔታ በማጣጣም ተፈፃሚነታቸውን መከታተል፣
- ከክልሉ መንግስት፣ ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ ከዞን፣ ከወረዳና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሠራርን በማጠናከር ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መሳካት በጋራ መሥራት፣
- ለዞን ጤና መምሪያ/ልዩ ወረዳ የቴክኒክና አስተዳደራዊ ድጋፍ መስጠት፣

- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በክልሉና ከክልሉ ውጭ የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎች በመቀመር እንዲስፉ ማድረግ፣
- በየስድስት ወሩ በየደረጃው ያሉ አካላትንና አጋሮችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ በማዘጋጀት በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላላቸው አካላት እውቅናና ማበረታቻ መስጠት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሥራ ላይ ስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ፤ አፈፃፀሙን መከታተል፣
- በተለያዩ ምክንያቶች ሥራቸውን በለቀቁ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ምትክ የማሟያ ስልጠና ማካሄድ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈጻጸም ላይ ጥናቶችን ማካሄድ/መደገፍ፣
- የድጋፋዊ ክትትል ሥራዎችን ማከናወን፣ ከሌሎች ክልሎች ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ የተሻለ አሠራርመዘርጋት፣
- የጤና አጠባበቅ መርጃ መሳሪያዎችንና የማጣቀሻ መጽሐፎችን ማዘጋጀት፣
- ለፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየወቅቱ ሪፖርት ማድረግ፣ የሚሰጠውን ግብረ መልስ በመጠቀምም ፕሮግራሙን ማሻሻል፣

### የዞን ጤና መምሪያ/ ልዩ ወረዳ/ክፍለ ከተማ ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ለማስፈፀም ልማት ሠራዊት ግንባታን ቁልፍ ተግባሩ አድርጎ መንቀሳቀስ፣
- በዞንና በወረዳ የተዋቀሩ ኮማንድ ፖስቶችን መደገፍ፤መከታተል፤ የመረጃ ልውውጥ ማድረግና በቅንጅት መሥራት፣
- የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሀድን መደገፍ፤መከታተል፤
- በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ርና በክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ የሚወጡ መመሪያዎችንና ደንቦችን ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ከዞን መስተዳደር ምክር ቤት፣ ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ ከወረዳና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሠራርን በማጠናከር ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መሳካት በጋራ መሥራት፣
- ለወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ መስጠት፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲስፉ ማድረግ፣
- በየሩብ አመቱ በየደረጃው ያሉ አካላትንና አጋሮችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ በማዘጋጀት በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላላቸው አካላት እውቅናና ማበረታቻ መስጠት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የስራ ላይ ስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ፤ አፈፃፀሙን መከታተል፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰልጣኞችን የማሟያ ምልመላ ማገዝና ማስተባበር፣
- የድጋፋዊ ክትትል ሥራዎችን ማከናወን፣
- የጤና አጠባበቅ መርጃ መሳሪያዎችንና የማጣቀሻ መጽሐፎችን ማዘጋጀት፣
- ለክልል ጤና ቢሮዎች በየወቅቱ ሪፖርት ማድረግ በሚሰጠውን ግብረ መልስ በመጠቀምም ፕሮግራሙን ማሻሻል፣

## የወረዳ ምክርቤትና አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት

- ልማት ሠራዊትግንባታን መምራት፣መከታተልና አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣
- ለመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ በቂ በጀት መመደብና አጠቃቀሙን ክትትል ማድረግ፣
- የተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች መካከል ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖር አቅጣጫ መስጠትና ለጤና ሴክተር የሚሰጠውን ድጋፍ ማጠናከር፣
- የግብዓቶችና መድኃኒቶች አጠቃቀም መቆጣጠር እንዲሁም በቂ የሰው ሀይልና በጀት መመደብ፣
- በወረዳው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበርን በየጊዜው መገምገም

## የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ለማስፈፀም የልማት ሠራዊት ግንባታን ቁልፍ ተግባሩ አድርጎ መንቀሳቀስ፤ ወረዳውን በተደራጀ የህዝብ ንቅናቄ መምራት፣
- በወረዳና በቀበሌ የተዋቀሩ ኮማንድ ፖስቶችን መደገፍ፤መከታተል፤ የመረጃ ልውውጥ ማድረግና በቅንጅት መሥራት፣
- በወረዳው የሚገኙ ሁሉም ጤና ጣቢያዎች መደገፍ፤መከታተል፣
- በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ርና በክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ የሚወጡ መመሪያዎችንና ደንቦችን ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ከወረዳ መስተዳደር ምክር ቤት፣ ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሠራርን በማጠናከር ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መሳካት በጋራ መሥራት፤
- ለጤና ጣቢያዎች የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ መስጠት፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲስፋ ማድረግ፣
- በየሩብ አመቱ በየደረጃው ያሉ አካላትንና አጋሮችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ በማዘጋጀት በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላላቸው አካላት እውቅናና ማበረታቻ መስጠት፣ አስፈላጊ ግብአትም እንዲሟላ ማድረግ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የስራ ላይ ስልጠና መስጠት፤የሙያ ማሻሻያ ትምህርት እንዲያገኙ ምልመላ ማድረግ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰልጣኞችን የማሟያ ምልመላ ማካሄድ፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ኢንስፔክሽን/ድጋፍና ክትትል ማካሄድ፤ግብረ መልስ መስጠት፣
- ለክልል ጤና ጥበቃ ቢሮና ለዞን ጤና መምሪያ/ክፍለ ከተማ በየወቅቱ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ፣ የሚሰጠውን ግብረ መልስ በመጠቀምም ፕሮግራሙን ማሻሻል፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ቅጥር መፈፀም፤በተለያዩ ምክንያቶች የጎደሉትንም ማሟላት፤

## የማዘጋጃ ቤቶች፣ ፅዳትና ውበት ኤጀንሲዎች እስከ ቀበሌ ያሉ መዋቅሮች ተግባርና ሃላፊነት

- ከከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ጋር መሥራትና በጋራ የሃይጅንና ሳኒቴሽን ዘመቻዎችን እንዲሁም የህብረተሰብ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ሥራዎችን መሥራት፣
- ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማደራጀት ወይም የነበሩትን እንደገና በማንቀሳቀስ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ችግሮችን መፍታት
- በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ላይ የሚሰሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰሩትን እና በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እንዲሁም ሌሎች ሴክተሮችን ማገናኘትና ማቀናጀት
- እያደገ የመጣውን የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ችግሮችን ለዘለቄታው መፍታት የሚችል እና ኤጀንሲው ለሰጠው አገልግሎት የሚሆን የክፍያ ሥርዓት ማዘጋጀት
- ከተዘረጉት የከተማ ጤና መዋቅሮች ጋር በመሆን ከሌሎች ሴክተሮች ጋር ላለው መተባበር፣ውህደት እና መናበብ እንዲሁም ተከታታይ ስብሰባዎችን በመሳተፍ አብሮ መሥራት
- የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ አገልግሎት ቀልጣፋና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎችን ማዕከል ያደረገ እንዲሆን ማድረግ
- የግል ድርጅቶች በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ አገልግሎት ላይ ተሳታፊ የሚሆኑበት ሥርዓት መዘርጋት
- የፍሳሽ ቆሻሻ እና የአይነ ምድር ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገድ አገልግሎት መስጠት
- ህብረተሰቡ ንፁህና በቂ ውሃ ለመጠጥና ለቤት አገልግሎት በአለም የጤና ድርጅት መስፈርት መሠረት መድረሱን ማረጋገጥና በጋራ የውሃ ጥራት ቅኝት ማካሄድ እና የቅኝቱን ውጤት ከሚመለከተው ጋር መለዋወጥ
- ከሚመለከታቸው ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ዲዛይንና ግንባታ በትክክል መከናወኑን እንዲሁም ለተጠቃሚው ምንም አይነት የጤና ችግር የማያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ
- በማዘጋጃ ቤት/በድርጅቶች የሚሰጠውን የፍሳሽ ቆሻሻ መምጠጥ አገልግሎት የጤና ተቋም የሃይጅን ቡድን እና ሌሎች ሴክተሮች ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር ማቀናጀት
- የህዝብ መፀዳጃ ቤቶችን፣የጋራ መፀዳጃ ቤቶችን እንዲሁም የህዝብ የውሃ ተቋማትን በሚፈለጉበት ቦታ ማቅረብና በከተማው ውስጥ እነዚህን ተቋማት የማስተዳደር ስርዓቱን ማሻሻል

## የደንብ አስከባሪ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

- በማህበረሰቡ ጤና ላይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ሥራዎችን ማለትም የግልና የአካባቢ ንፅህና ዘመቻና የማህበረሰብ ንቅናቄ ላይ ከከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ጋር በጋራ በመሆን መሥራት፣
- ህገ ወጥ በሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ላይ መደበኛ የሆነ ክትትል ማድረግ፣
- ማህበረሰቡ በተከለከሉ ቦታዎች ላይ ቆሻሻዎችን እንዳያስወግድ የግልና የአካባቢ ንጽህናን በተመለከተ የተቀመጡ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- በከተማ ውስጥ በተፈጠሩ የጤና መድረኮች ላይ በቅንጅት ለመሥራትና ትብብር ለመፍጠር መሥራት፤ ስብሰባዎችን በቋሚነት መሳተፍ፣
- ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች  በጋራ መሥራት፣

**የዩንቨርሲቲዎች ተግባርና ሃላፊነት**

- ማህበረሰብ አቀፍ የጤና አገልግሎት ፍላጎትና አጠቃቀም ላይ በተለይም (የከተማ ጤና አገልግሎት፣ የሪፈራል አገልግሎቶች መኖር፣ አገልግሎቶቹን የመጠቀም ልምድና የሚያጋጥሙ ማነቆዎች/መሰናክሎች) ላይ የምርምር ርዕሶችን መለየት፣
- መሰረታዊ የከተማ ጤና ርዕሶችን በተለይም የከተማ ጤናን የሚወስኑ ነገሮች፤የተጋላጪነት ዳሰሳ ጥናት፤ የጥራት አመላካቾችን እንደ(ተደራሽነት፤ሞዴል አገልግሎት) የመሳሰሉትን በተመለከተ ፤ የትምህርት ተቋማት ጤናና የዕፅ አጠቃቀም) ላይ ምርምር ማካሄድ
- የአገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል ለከተማ ጤና አገልግሎት አቅራቢዎች የሚሆን ብቃትን መሠረት ያደረገ ስልጠና ማዘጋጀትና መስጠት፣

**የቀበሌ ምክርቤትና አስተዳደር ተግባርና ሀላፊነት**

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ለማስፈፀም ልማት ሠራዊት ግንባታን ቁልፍ አጀንዳ አድርጎ መንቀሳቀስ፤
- የቀበሌውን የሠራዊት ግንባታ ለመከታተልና ለመደገፍ ኮማንድ ፖስት ማቋቋም፣
- የልማት ቡድኖችንና የ1ለ5 ትስስሮችን አባላት በቋሚነት መሰብሰብ፣መከታተል፣መደገፍና መገምገም፤
- በቀበሌው ያሉ የልማት ቡድንና የ1ለ5 ትስስሮችን ሥራዎች መረጃዎችን መሰብሰብ፤መተንተን፤

**የት/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት**

- በትምህርት ቤት ሊተገበሩ የሚችሉ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን መተግበርና ለፕሮግራሙ ስኬታማነት ከጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያች ጋር መሥራት፣
- በትምህርት ቤት የጤና ክበብ በማቋቋም የጤና ትምህርት መስጠትና በሕብረተሰቡ የሚተገበሩ የጤና ልማት ሥራዎችን መደገፍ፣
- መደበኛውን የትምህርት ሂደት በማያስተጓጉል መልኩ በተማሪዎች የጠዋት ሰንደቅ ዓላማ ስነ-ስርዓት ላይ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በሳምንት የተወሰነ ሰዓት በትምህርት ቤት ስለጤና አጠባበቅ ትምህርት የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- የተለያዩ የጤና ተግባራትን የሚያመለክቱ ስንታንዳርዱን በጠበቀ መለኩ በት/ቤት በማዘጋጀት (መፀዳጃ ቤት፣የእጅ መታጠቢያ፣የቆሻሻ ጉድጓድ፣ወዘተ.) እንዲጠቀሙ በማድረግ የተማሪዎችን ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ፣

**የሴቶች አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት**

- በልማት ሠራዊት ግንባታ ሂደት በግንባር ቀደምትነት መንቀሳቀስ፣
- አባላቶቻቸውን በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ሞዴል እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ለልማት ቡድንና ለ1ለ5 ትስስር አባላት ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣
- በየደረጃው ካሉ የጤናው ሴክተር አካላት ጋር ተባብሮ መሥራት፣
- በዕቅድ ዝግጅት አተገባበርና ግምገማ ላይ መሳተፍ፣

**የአጋር ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት**

- ከፌዴራል ጀምሮ እስከ የመጀመሪያ የጤና ክብካቤ አሀድ ባሉ የጤና መዋቅሮች ፍላጎት መሠረት ለፕሮግራሙ መሳካት አስፈላጊውን ሁሉን አቀፍ ድጋፍ መስጠት፣

**የጤና ጣቢያው ኃላፊዎች ተግባርና ሃላፊነት**

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ለማስፈፀም የጤና ልማት ሠራዊት ግንባታን ቁልፍ ተግባሩ አድርጎ መንቀሳቀስ፤በስሩ ያሉ ቀበሌዎችን በተደራጀ የህዝብ ንቅናቂ መምራት፣
- በስሩ ላሉ ጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎች ድጋፍ መስጠት፤ መከታተልና መገምገም፣

- የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሀድ የጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎችን ጨምሮ ዕቅድን ማዘጋጀት፣
- በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት በአመለካከት፣ በክህሎትና በግብዓት አቅርቦት ያሉትን ማነቆዎች በመለየት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማስፈፀም፣
- በጤና ጣቢያው ሥር ባሉ ቀበሌዎች/ቀጠናዎች ያሉ የልማት ቡድንና የ1ለ5 ትስስሮችንና ሌሎች ጤናና ጤና ነክ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ለዕቅድ ዝግጅትና ክለሳ መጠቀም፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎች በመቀመር በራሳቸው ሥር ባሉ ቀበሌዎች በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እንዲስፋፉ ማድረግ፣
- በየሳምንቱ በሥሩ ካሉ ጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎች ጋር የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሥራ ላይ ስልጠና መስጠት፣
- በጤና ጣቢያ የሚገኙ ባለሙያዎች ቀበሌዎችን በመከፋፈል የጤና ልማት ሥራዎችን ቀበሌ ወርደው እንዲደግፉ ማድረግ፣
- ለወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በየወቅቱ ሪፖርት በማዘጋጀት ማቅረብ፣

## በጤና ጣቢያ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ተጠሪ ባለሙያ (Focal Person) ተግባርና ኃላፊነት

የጤና ኤክስቴንሽን ተጠሪ ባለሙያ ተጠሪነቱ ለጤና ጣቢያ ሀላፊ ሆኖ በጤና ጣቢያው ሥር ላሉ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ድጋፋዊ ክትትል በማከናወን ረገድ የሚከተሉትን ተግባራት ይፈጽማል፡፡

- የመሠረታዊ ጤና ክብካቤ ፕሮግራም ዕቅድ ከሀላፊው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣
- በጤና ጣቢያው የሚገኙ ባለሙያዎችን ለጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎች የሚያደርጉትን የድጋፍ ዓይነት ከጤና ጣቢያ ሀላፊ ጋር በመነጋገር ይለያል፣ ድጋፍ እንዲደረግ ፕሮግራም ያወጣል፣ መፈፀሙን ይከታተላል፣ ሪፖርት ለዳይሬክተሩ ያቀርባል፣
- በፕሮግራሙ ላይ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያጠናክራል፣ ሁሉን አቀፍ የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣
- የድጋፋዊ ክትትል ሥራዎችን እለት በዕለት ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይፈፅማል፣
- ለጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎች አስፈላጊው ግብዓት መሟላቱን ይከታተላል፡፡
- ለእያንዳንዱ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የመሥሪያ ክልል/ቀጠና መመደብ
- የድጋፍ አሰጣጡን ሂደት ለመከታተል ሳምንታዊ ስብሰባ በጤና ጣቢያ ደረጃ እንዲኖር ያስተባብራል
- ለጤና ጣቢያው ቦርድ፣ለጤና ጣቢያው ዳይሬክተር እና ለሌሎች አጋሮች የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አካሄዶችና ችግሮችን በሚመለከት ያስገነዝባል፡፡

## ሌሎች የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት

- እያንዳንዱ ባለሙያ የራሱ ቀበሌ/ቀጠና ይይዛል፤ በሚደግፈው ቀበሌ የልማት ሠራዊት የማደራጀትና የማጠናከር ሥራዎችን ይደግፋል፤ይከታተላል፣

- እያንዳንዱ ባለሙያ በተመደበበት ፕሮግራም መሠረት ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ በቤት ለቤት ጉብኝት፣ት/ቤትና በወጣት መዕከላት በመገኘት ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፣
- በጉብኝት ወቅት በእያንዳንዱ ፓኬጅ አፈፃፀም ላይ ያሉትን የአመለካከት፣ የክህሎትና የግብዓት አቅርቦት ማነቆዎች በመለየት፣ በተለዩት ላይ በግንባር ድጋፍ ይሰጣል፣ ግብረ መልስም ያዘጋጃል፣
- ሥራዎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሠረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣ ችግር ሲኖርም አስፈላጊውን ማስተካከያ ሰርቶ ያሳያል፣
- በልማት ቡድንና 1ለ5 ስልጠና ላይ በመገኘት ከጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎች ጋር በመሆን በሙያው ስልጠና ይሰጣል፣
- የተከናወኑ ሥራዎች በአግባቡ መመዝገባቸውን፣ ሪፖርት መደረጉንና የተደረገው ሪፖርት ካለው መረጃ ጋር መገናዘቡን ያረጋግጣል፣
- በሙያዊ ድጋፍና ክትትል ወቅት ስላከናወነው ተግባር ለፎካል ባለሙያ ሪፖርት ያደርጋል፤
- በየሳምንቱ በጤና ጣቢያ በሚደረገው የሥራ ግምገማ ውይይት ላይ ይሳተፋል፡፡

**የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት**

- የሴቶች ልማት ሠራዊትን ማሰልጠን፣ መከታተል
- ከጤና ጣቢያ፣ ቀበሌ አስተዳደርና ሌሎች አካላት ጋር በመሆን ዕቅድ ማዘጋጀት፣ መተግበር፣ አፈፃፀሙን በጋራ መገምገም፣
- የልማት ቡድኖችንና የ1ለ5 ትስስሮችን አባላት በቋሚነት መሰብሰብ፣መከታተል፣መደገፍና መገምገም፤
- የቀበሌውን የጤና ዕቅድ በልማት ቡድን እና በ1ለ5 እንዲሁም በቤተሰብ ደረጃ መከፋፈሉን ማረጋገጥ፣
- አጠቃላይ የቀበሌውን ጤናና ጤና ነክ መረጃዎችን በመሰብሰብ መተንተንና ማጠናቀር እንዲሁም የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለጤና ጣቢያ ማድረግ፤
- በመደበኛነት የቤት ለቤት ጉብኝት ማድረግ እንዲሁም በማህበረሰብ የሚሠሩ ሥራዎችን ማከናወን፤
- ለፕሮግራሙ የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችን፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችንና ሌሎች ግብዓቶችን ጠይቆ ማሟላት፣ በመንግስት ንብረት አያያዝ ደንብ መሠረት መጠቀም፣
- በየሳምንቱ ለግማሽ ቀን ያህል በጤና ጣቢያ በሚደረገው የሥራ ግምገማ ላይ በመገኘት በፓኬጆች አፈፃፀም የሚስተዋሉ የአመለካከት፣የክህሎትና የግብዓት ማነቆዎችን በመለየት መፍታት/እንዲፈቱ ማድረግ፤
- የ1ለ5 መሪዎችን አባላትን ማሰልጠን፣ መከታተል፣ መደገፍና ብቁ ሲሆኑ በሞዴል ቤተሰብነት ማስመረቅ፣
- የ1ለ5 መሪዎች /አባላትን የሚከታተሏቸውን ቤተሰቦች መከታተልና መደገፍ ብቁ ሲሆኑ በሞዴል ቤተሰብነት ማስመረቅ

## 8. የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የድጋፍና ክትትል ማዕቀፍ

የክትትልና ግምገማ ሥርዓት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- የከተማ ጤና ኤክስቴንሽ ፕሮግራም አፈጻጸምን በተከታታይ ለማጤን
- መረጃ በመሰብሰብ፣በማጤን/መተንተን፣በመጠቀምና የመረጃ ጥራትን በመጠበቅ በኩል እቅድ እንዲታቀድ
- የተለያዩ ዘዴዎችን በማውጣት/በመቅረጽ መረጃን መሠረት ያደረገ ውሳኔ መስጠት

### 8.1 መረጃዎችን በቋሚነት መመዝገብና ሪፖርት ማድረግ (Automated)

ሥራዎችን በተደጋጋሚ ከመሥራት ለማስቀረትና ግብዓትን በአግባቡ ለመጠቀም የአሠራር ሥርዓቱ የጤና ተቋምን መሠረት ያደረገ መረጃን የመያዝና ሪፖርት የማድረግ አሠራር (HMIS) ይከተላል፡፡ የመረጃ መመዝገቢያና ሪፖርት ቅጾች በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አስተባባሪነት የሚዘጋጁ ሲሆን የፕሮግራሙን ውጤታማነት በትክክል ለመከታተል የሚያስችል ሆኖ ይዘጋጃል፡፡ በዚህም የሚገኘውን መረጃ ለውሳኔ አሰጣጥ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በየደረጃው የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ወደ ሚቀጥለው የጤና እርከን ከማስተላለፍ በተጨማሪ የተሰበሰበውን መረጃ በመጠቀም የውስጥ ግምገማ ማካሄድ፣ ማነቆዎችን መለየትና አስፈላጊውን የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

### 8.2 በቋሚነት መገምገም (Periodic reviews)

***ሣምንታዊ ግምገማ (Weekly review):*** ግምገማው በጤና ጣቢያ ደረጃ ሁሉም የጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎችና ድጋፍ የሚሰጡ ባለሙያዎች የሚካሄድ ይሆናል፡፡ እነዚህ ግምገማዎች ተሞክሮዎችን የሚቀምሩበት/የሚይዙበትና በቡድን መካከል የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚረዱ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም ለሚቀጥለው/ለመጭው ሳምንት ዕቅድ ለማዘጋጀትና ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለማፍታት መፍትሄ ለማፈላለግ ይጠቅማል፡፡

በዞን/ክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ በየሩብ ዓመቱ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣ጤና ጣቢያዎችን፣ የሴቶች አደረጃጀቶችንና አጋሮችን ያሳተፈ የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ ይካሄዳል፡፡ በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላላቸው አካላት እውቅናና ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

በክልል ደረጃም በየግማሽ ዓመቱ በየደረጃው ያሉ አካላትንና አጋሮችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ በማዘጋጀት በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላላቸው አካላት እውቅናና ማበረታቻ ይሰጣሉ፡፡

በፌዴራል ደረጃ በየዓመቱ ሁሉንም ክልሎችና አጋር ድርጅቶችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ይካሄዳል፡፡ በዚህም በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም የተሻለ ደረጃ ላላቸውና የላቀ አስተዋፅዖ ላበረከቱ አካላት እውቅናና ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

በየደረጃው ከሚካሄዱ የአፈፃፀም ግምገማዎች በተጨማሪ በራስ ተነሳሽነትና በገለልተኛ አካላት በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም ላይ ጥናቶችን በማስጠናትና በሌሎች አካላት የተደረጉ ጥናቶችን በመጠቀም በፕሮግራሙ ላይ ቀጣይነት ያለው የማሻሻያ ስራ ይሰራል፡፡ ለምሳሌ፡-

- በከተማው ማህበረሰብ ላይ የመጡት ለውጦች ምን ምን ናቸው? በከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የተሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ ምን ያህል ዓላማዎችን እንዳሳኩ

ለመለየት፤ ይህ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሥራቸውን ውጤታማነት በተመለከተ ግምት ለመስጠት ያግዛቸዋል፡፡

- በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች ጥራት ምን ይመስላል?
- በመሠረታዊ የጤና ክብካቤ አሃድ ደረጃ የጤና አገልግሎት በፍትሃዊነት መጠቀም (Equity) ምን ይመስላል?

## 8.3 ድጋፋዊ ክትትልና ኢንስፔክሽን

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የታለመለትን ግብ ለማሳካት በየደረጃው የተጠናከረና ቀጣይነት ያለው ድጋፍና ክትትል ማካሄድ ወሳኝ ነው፡፡ በቀበሌ ደረጃ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከልማት ቡድኖችና ከ1ለ5 ትስስር መሪዎች ጋር በየጊዜው በመገናኘት በፓኬጆች አፈፃፀም በተለይም ትኩረት በሚሰጣቸው የጤና አገልግሎቶች ላይ በመወያየት አፈፃፀማቸውን ይገመግማሉ፤ በዚህ ሂደትም የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን በአመለካከት፣ በክህሎትና በግብዓት በመተንተን መፍትሔዎችን ያስቀምጣሉ፡፡

በጤና ጣቢያ ደረጃ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በስራቸው ያሉ ቀበሌዎችን/ቀጠናዎችን በመከፋፈል በየሳምንቱ በቼክሊስት በመታገዝ ይደግፋሉ፡፡ የሚካሄዱ ድጋፍና ክትትሎችም በፓኬጆች አፈፃፀም የሚታዩ የአመለካከት፣ የክህሎትና የግብዓት ማነቆዎችን የሚፈቱ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ ዳይሬክተርም የድጋፍና ክትትል ሥራውን በበላይነት ያስተባብራል፤ ይመራል፡፡

የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ደረጃ ቢያንስ በየወሩ ወጥ የሆነ ቼክሊስት በመጠቀም ለጤና ጣቢያዎችና ጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎች ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፡፡ በድጋፍና ክትትሉ ለተለዩት ማነቆዎችም አስፈላጊውን የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፡፡

የዞን/ክፍለ ከተማ ጤና መምሪያ፣ ከክልል ጤና ቢሮና ፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር በመቀናጀት ወጥ የሆነ ቼክሊስት በመጠቀም የዞኖችን/ክፍለ ከተማ፣ የወረዳዎችን፣ የጤና ጣቢያዎችን በአፈፃፀም ደረጃቸው በመለየት ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፡፡ ይህ በቅንጅት የሚደረገው ድጋፍና ክትትል በየደረጃው የተለዩ ማነቆዎችን ማን በባለቤትነት መፍታት እንደሚገባው ኃላፊነት ለመስጠት፣ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም ላይ ተመሳሳይ አረዳድ ለመያዝ እንዲሁም በሚደረጉ ድጋፍና ክትትሎች ባጭር ጊዜ ብዙ ዞኖችን፣ ወረዳዎችንና ጤና ተቋማትን ለመሸፈን ጠቀሜታው የላቀ ነው፡፡

በየደረጃው የሚደረግ ድጋፍና ክትትል ሶስቱን የድጋፍና ክትትል ማዕቀፎችን (ሪፖርት፣ ኢንስፔክሽንና ግብረመልስ) ተከትሎ ሊደረግ ይገባል፡፡ በዚህም መሠረት ድጋፍና ክትትል የሚያደርገው አካል ወደ መስክ ከመውጣቱ በፊት ድጋፍ ስለሚሰጠው አካል የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን በመገምገም ትኩረት መስጠት ያለበትን የጤና አገልግሎቶች መለየት፤ እስከ ቤተሰብ ድረስ በመውረድ ሪፖርት የተደረጉ ሥራዎች ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥና ግኝቱን ለሚመለከተው ሁሉ ግብረመልስ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ በድጋፍና ክትትሉም ወቅት በየደረጃው ያሉ ማነቆዎችን ከመለየትና መፍትሔ ከማፈላለግ በተጨማሪ ምርጥ ተሞክሮዎችን የመቀመርና የማስፋት ሥራ መሥራት ይኖርበታል፡፡

ከድጋፋዊ ጉብኝት ጎን ለጎን በየደረጃው ያለው አመራር እንደ አከባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ወደ ታች በመውረድ የተሰሩ ሥራዎችና ሪፖርት የሚደረገውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኢንስፔክሽን ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡

## 8.4 የከተማ ጤና ኤክስቴሽን ፕሮግራም ስኬታማነት አመላካቾች

## ግብዓት/INPUTS

- የሰለጠኑ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች
- የመድሃኒትና የህክም መገልገያዎች
- የጤና ኤክስቴንሽን የማስፈፀምያ ሰነዶች
- ፋይናንስ
- የአምቡላንስ አገልግሎት
- የጤና መሰረተ ልማት አውታሮች
- የህብረተሰብ ተሳትፎ

## ተግባራት/PROCESS

- ለከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አስፈላጊውን ቁሳቁሶችን ማሟላት
- ለከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት
- ክትትልና ድጋፍን ማጠናከር
- ምርጥ ተሞክሮችና ልምዶችን መለየትና ማስፋት
- ቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከር
- ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት
- ሪፈራል ሥርዓትን ማጠናከር

## Out put

- የተሻሻለ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ክህሎት
- ደረጃዎችን የጠበቀ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያዎችና ማኑዋሎች
- የተሻሻለ የሪፈራል ትስስር
- በደንብ የተብራሩ ደረጃቸውን የጠበቁና የተቀናጁ ፓኬጆች መረጃዎች አሰባሰብ፣ ትንተናና አጠቃቀም መሻሻል

ጥራት ያለው አገልግሎት

## ውጤት/OUTCOME

- ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ተደራሽነት መጨመር
- አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር መጨመር

## ፋይዳ/IMPACT

- የራሱን ጤና ያመረተ ህብረተሰብ

**ፍትሃዊነትና ጥራት**

**ከፕሮግራም ትግበራ የሚጠበቁ ውጤቶች**